የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ ኅዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፪

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

6th Year No. 3
ADDIS ABABA - 18th November, 1999


## ማውጫ


አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፩/፲፱፻፺፪ ዓ.ም.
ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅትን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ለማስተላለፍ የወጣ አዋጅ ........................................ ገጽ ፩ሺ፩፻፸፫


## CONTENTS


Proclamation No. 181/1999
Transfer of the Monopoly Right of the National Tobacco Enterprise to the National Tobacco Enterprise (Ethiopia) share Company proclamation ........................................ Page 1173


### አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፩/፲፱፻፺፪
### ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅትን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ለማስተላለፍ የወጣ አዋጅ

ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅት በከፊል ወደ ግል ይዞታ የተዛወረና ወደ አክሲዮን ማኅበርነት የተለወጠ በመሆኑ ፤

ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ ተሰጥቶት የነበረውን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ማስተላለፍ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅትን የሞኖፖሊ መብት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ለማስተላለፍ የወጣ አዋጅ ቁጥር ፩፻፹፩/፲፱፻፺፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· <u>የሞኖፖሊ መብት መተላለፍ</u>

፩· ትምባሆና የትምባሆ ውጤቶችን ለመግዛት ፣ ለመቀመም፣ በፋብሪካ ሠርቶ ለማውጣት ፣ ለመሸጥ ፣ ወደአገር ውስጥ ለማስገባትም ሆነ ወደውጭ ለመላክ ለብሔራዊ የትምባሆ ድርጅት በማቋቋሚያው አዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፬ በአንቀጽ ፪ እና ፱ ድንጋጌዎች መሠረት ተሰጥቶት የነበረው የሞኖፖሊ መብት በዚህ አዋጅ ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር ተላልፏል ።

### PROCLAMATION No.181/1999
### A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR THE TRANSFER OF THE MONOPOLY RIGHT OF THE NATIONAL TOBACCO ENTERPRISE TO THE NATIONAL TOBACCO ENTERPRISE (ETHIOPIA) SHARE COMPANY

WHEREAS, the National Tobacco Enterprise has been partially privatized and converted into a share company;

WHEREAS, it has become necessary to transfer the monopoly right of the National Tobacco Enterprise, as stipulated by its establishment proclamation, to the National Tobacco Enterprise (Ethiopia) Share company;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Transfer of the Monopoly Right of the National Tobacco Enterprise to the National Tobacco Enterprise (Ethiopia) share Company proclamation No. 181/1999."

2. *Transfer of Monopoly Right*

1) The Monopoly right of the National Tobacco Enterprise in respect of the purchase, preparation, manufacture, sale , import and export of tobacco and tobacco products, as stipulated in Article 2 and 9 of its establishment proclamation No. 37/1992, is hereby transferred to the National Tobacco Enterprise (Ethiopia) Share Company.

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ መሠረት ለብሔራዊ ትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር የተላለፈውን የሞኖፖሊ መብት ለማስከበር አግባብ ያላቸው የአዋጅ ቁጥር ፴፯/፲፱፻፹፭ አንቀጽ ፲—፲፫ ድንጋጌዎች ተፈጻሚነት ይቀጥላል ፡፡

፫· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ብሔራዊ የትምባሆ ድርጅት (ኢትዮጵያ) አክሲዮን ማኅበር በንግድ መዝገብ ከተመዘገበበት ቀን ጀምሮ ቢያንስ ለአሥር ዓመታት ጸንቶ ይቆያል ፡፡

አዲስ አበባ ህዳር ፰ ቀን ፲፱፻፺፪ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

2) The relevant provisions of Articles 10-13 of Proclamation No. 37/1992 shall remain in force and apply to the enforcement of the monopoly right transferred to National Tobacco Enterprise (Ethiopia) Share Company pursuant to Sub-Article (1) of this Article.

3. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the date of registration of the National Tobacco Enterprise (Ethiopia) Share Company in the commercial register and shall remain in force at least for 10 years thereafter.

Done at Addis Ababa, this 18th day of November, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE